(3) አድራጊ ሁን ፣ እንደ ቃሉ ተግብር

እግዚአብሔር ቃሉን ሰሚ ብቻ እንድንሆን አይወድም ነገር ግን አድራጊዎች እንድንሆን እንጂ ***'' ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናቹ እራሳችሁን ኣታታልሉ። ቃሉን የሚሰማ ነገር ግን የማይተገብር ቢኖር ፊቱን በመስተዋት እንደ ሚያይ ሰው ነው፤ ራሱን ኣይቶ ይሄዳልና፥ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸና፥ የሰማዉን የሚያደርግና የማይረሳ ሰው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል"*** (የያዕቆብ መልእክት 1:22 -25)።

ቃሉን አስታዉሰህ እንደ ሚለው ከፈጸምክ ቃሉን አድራጊ ትሆናለህ። እናም ሁልጊዜም ቢሆን ታስታዉሳለህ ይህም መንፈስ ቅዱስ በዉስጣችን ሆኖ ከሚያደርገው ከብዙዎቹ አንዱ ነው። እየሱስ እንዳለው *''እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል"* (ዮሓንስ 14:26)። እግዚአብሔር ይመስገን መንፈስ ቅዱስ አሁን ከኛ ጋር አለ፤ ቃሉን እንድናስታዉስ ያግዘናል! ቃሉንም ባስታወስክ ጊዜ፣ ልትፈጽመው ይገባል። ስለማስታወሱ አትጨነቅ ፤መንፈስ ቅዱስ ወደ ማስታወስህ ያመጣኃል፣ ነገር ግን ሁልጊዜ እዉነትን ወደ ልብህ ባመጣበት ጊዜ ልትታዘዘው ዝግጁ ልትሆን ይገባል።

(4) አስታዉስ ኃጢአት ባንተ ላይ ስልጣን የለዉም

አንድ ነገር ልታስታዉስ ይገባሃል፣ እነዚህ ሃሳቦች ባንተ ላይ እንዲሰለጥኑ ካልፈቀድክላቸው በስተቀረ፣ ምንም ኃይል የላቸውም *''ኃጢአት ኣይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ኣይደላችሁምና''* (ወደ ሮሜ ሰዎች 6:14)። ኃጢአት ባንተ ላይ ጌትነትን ሊያገኝ አይገባውም፣ የበላይ ስልጣንም አይኖረዉም ምክንያቱም አንተ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለህምና። መጽሓፍ ቅዱስም ይህንን ነው የሚለው ።

እግዚአብሔር ከኃጢአት ስልጣንና ከጨለማው ኃይል አድኖኃል ወደሱም መንግስት አሻግሮኃልና፤ ***''በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ወደ ዉድ ልጁ መንግሥትም አሻገረን"*** (ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:12-13) ።

ዳግመኛ ከተወለድክ በኋላ አንተም በዚያ አትኖርም፣ ለዛም ነው የጨለማው ኃይሎች ባንተ ላይ ስልጣን የሌላቸው። ምክንያቱም እነርሱ በኃጢአት ግዛት ዉስጥ ስላሉ፣ አንተ ግን በእግዚአብሔር ግዛት ዉስጥ ስላለህ፣ ይህም ከኃጢአት የበለጠ (የበላይ) ስለሆነ። ስለዚህ አየህ፣ በምንም አይነት ባንተ ላይ ስልጣን አይኖራቸውም ።

ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:14 እንዲህ ይላል፣ ***''በእርሱም በደሙ የሆነ መዋጀትን አግኝተናል፣ ይህም የኃጢአት ይቅርታ ነው"*** ። ***''በእየሱስ ክርስቶስ ተዋጅተናል ይህም በአሁን ጊዜ ያለን ጸጋ ነው"*** (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:5-6)። ለማግኘት እየጣርን አደለንም፣ አሁን ጸጋው አለን። ይህን የእግዚአብሔርን ቃል ማስታወስ አለብን፣ በዛም ልንጽናና ይገባል።